# የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ

## ETHIOPIAN HUMAN RIGHTS COUNCIL

ኢሰመጉ የቆመው ለዲሞክራሲ፣ ለሕግ ልዕልናና ለሰብአዊ መብቶች መከበር ነው፡፡

**EHRCO** stands for democracy, the rule of law and the respect of human rights.

ህዳር 19 ቀን 2000 ዓ.ም

## 104ኛ ልዩ መግለጫ

## የተማሪዎች የመሰማት መብት ይከበር!

### መግቢያ

ኢትዮጵያ ፈርማ የተቀበለችው የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና የባህል መብቶች ቃልኪዳን አንቀጽ13(1) እያንዳንዱ ሰው ትምህርት የማግኘት መብት እንዳለው ያረጋግጣል፡፡ ትምህርት የሰውን ሰብዕናና ክብር በማሳደግ ለሰብአዊ መብቶች መከበር አስተዋጽኦ ማድረግ እንደሚገባውም ይህ አንቀጽ ያሰምርበታል፡፡ የኢፌዲሪ ህገ-መንግስትም በአንቀጽ 41 ስር ሁሉም ኢትዮጵያዊ ሙያውን የመምረጥ መብት እንዳለው ይደነግጋል፡፡ ሰዎች ይህንን መብታቸውን በተሟላ መልኩ ሊጠቀሙበት የሚችሉት ደግሞ አስፈላጊውን ትምህርት ሲያገኙ በመሆኑ መንግስት ሁሉንም ዜጎች ተጠቃሚ የሚያደርግ የትምህርት አገልግሎት ማስፋፋት እንዳለበት ህገ-መንግስቱ ከላይ በተጠቀሰው አንቀጽ ስር ያረጋግጣል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ማንኛውም ሰው በህግ እውቅና ያገኙት መብቶቹ በህግ ከተደነገገው ውጪ እንዳይጣሱበት መጠበቅ መሰረታዊ የህግ የበላይነት መርህ የሚጠይቀው ግዴታ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር በወንጀል የተጠረጠረም ሆነ ማንኛውን የዲሲፕሊን ጥፋት ፈጽሟል የተባለ ሰው የቀረበበትን ክስ የማወቅ፣ የቀረበበትን ማስረጃ የማስተባበል፣ ይግባኝ የማለትን የመሳሰሉ እጅግ መሰረታዊ መብቶች አሉት፡፡ ጥፋተኝነቱ በፍ/ቤት ሳይረጋገጥበትም ጥፋተኛ ሊባል እንደማይቻል ይኸው ሕገ መንግሥት በግልጽ ደንግጓል፡፡

ይሁን እንጂ ከዚህ ህገ-መንግስታዊና አለምአቀፋዊ መርህ በተቃራኒ ከህግና ሥርዓት ውጭ ክስ ሳይቀርብባቸው ወይም ጥፋታቸው ምን እንደሆነ እንኳን ሳይገለጽላቸው የክረምት የእረፍት ጊዜያቸውን ከቤተሰቦቻቸው ጋር አሳልፈው ቀሪ ትምህርታቸውን ለማጠናቀቅ ሲመጡ ትምህርታቸውን እንዳይቀጥሉ የተወሰነባቸው በመሆኑ ወደ ግቢው መግባት እንደማይችሉ በጥበቃ ሰራተኞች እንደተነገራቸው አንዳንድ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ለኢሰመጉ አመልክተዋል፡፡ በሌላም በኩል በዚሁ ዩኒቨርሲቲ ባለፈው ዓመት ተመርቀን የትምህርት ማስረጃ ተከለከልን በማለት ሌሎችም ምሩቃን አመልክተዋል፡፡

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ(ኢሰመጉ) በዚህ 104ኛ ልዩ መግለጫው በማናውቀው ምክንያት ትምህርታችንን እንዳንቀጥል ተወሰነብን ሲሉ ባመለከቱ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችና የትምህርት ማስረጃ ተከለከልን ሲሉ ተመራቂዎች ያቀረቡትን ማመልከቻ መሰረት በማድረግ ጉዳዩን አጣርቶ እንደሚከተለው አቅርቧል፡፡

## ዝርዝር

1. ታደሰ ድንቁ ነዋሪነቱ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 13 የቤት ቁጥር 483 ውስጥ የሆነ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በመደበኛው ትምህርት መርሀ ግብር የ4ኛ አመት የግራፊክ አርት የዲግሪ ተማሪ ሲሆን የክረምት የእረፍት ጊዜውን ከቤተሰቦቹ ጋር ቆይቶ ለ2000 ዓ.ም ትምህርቱን ለመከታተል ወደ ዩኒቨርሲቲ ሲመጣ ምክንያቱን ባላወቀው ሁኔታ ትምህርታቸውን እንዳይቀጥሉ ከተወሰነባቸው ተማሪዎች አንዱ እንደሆነ በጥበቃ ሰራተኞች እንደተገለጸለት፣ ወደ ዩኒቨርሲቲው ግቢ ገብቶ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ለመረዳት ቢፈልግም ሰርኩለር የተላለፈበት ስለሆነ መግባት እንደማይችል የተነገረው መሆኑን ለኢሰመጉ አመልክቷል።

2. ሸረፈዲን ኡመር ነዋሪነቱ በድሬደዋ ከተማ ቀበሌ 06 የቤት ቁጥር 583 ውስጥ የሆነ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በመደበኛው ትምህርት መርሀ ግብር የ2ኛ ዓመት የባዮሎጂ ዲፓርትመንት የዲግሪ ተማሪ ሲሆን የክረምት የእረፍት ጊዜውን በማጠናቀቅ ትምህርቱን ለመከታተል ወደ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሳይንስ ፋኩሊቲ ሲመጣ የዩኒቨርሲቲው የጥበቃ ሠራተኞች የትምህርት ቤት መታወቂያውን ከተቀበሉት በኋላ ትምህርታቸውን እንዳይቀጥሉ ከተወሰነባቸው ተማሪዎች አንዱ እንደሆነ ነግረውት ከአካባቢው ሊለቅ እንደቻለ እና በምን ምክንያት ሊባረር እንደቻለ ለማንስ አቤት ማለት እንዳለበት ማወቅ ባለመቻሉ በችግር ላይ እንደሚገኝ አመልክቷል።

3. አህመድ መሀመድ ቃዲ ነዋሪነቱ በአለማያ ከተማ በቀበሌ 01 መስተዳድር የቤት ቁ. 01/08 በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በመደበኛው የትምህርት መርሀ ግብር በስነ ምድር (ጂኦሎጂ)ዲፓርትመንት የዲግሪ ትምህርቱን ተከታትሎ በ1999 ዓ.ም የተመረቀ ሲሆን የትምህርት ማስረጃውን ለመውሰድ ወደ ዩኒቨርሲቲ ሲሄድ ምንም አይነት ምክንያት ሳይነገረው የጥበቃ ሠራተኞች የስም ዝርዝሩን ተመልክተው ወደ ዩንቨርስቲው መግባት እንደማይችል የትምህርት ማስረጃውም እንደማይሰጠው ከአካባቢውም እንዲርቅ አለበለዚያ የፌዴራል ፖሊስ ተጠርቶ በቁጥጥር ስር ሊውል እንደሚችል ተነግሮት ከዩኒቨርሲቲው አካባቢ ሊርቅ መቻሉን የትምህርት ማስረጃውን በምን ምክንያት እንኳን እንደተከለከለ አለማወቁን እና በማስረጃ እጦት ምክንያት ስራም ለመወዳደር አለመቻሉን አመልክቷል።

4. አበባው መሀመድ ነዋሪነቱ በደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን በጃማ ወረዳ በቀበሌ 01 የሆነ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በመደበኛው የትምህርት መርሀ ግብር ትምህርቱን በመከታተል በ1999 ዓ.ም በስታቲስቲክስ ዲፓርትመንት በዲግሪ የተመረቀ ሲሆን የትምህርት ማስረጃውን ለመውሰድ ወደ ዩኒቨርሲቲው ቅጥር ግቢ ሲሄድ ለጥበቃ ክፍሎች ስሙ እና ፎቶግራፉ ተበትኖ መግባትም ሆነ የትምህርት ማስረጃውን ማግኘት እንደማይችል ሰርኩለር የተላለፈ በመሆኑ አካባቢውን ለቆ እንዲሄድ ተነግሮት ከአካባቢው መሸሹን የተከለከለበትን ምክንያትም እንደማያውቅ እና በማስረጃ እጦትም ስራ እንኳን ለመወዳደር ባለመቻሉ ችግር ላይ መውደቁን አመልክቷል።

5. **ሞላ ፊሊጶስ ነዋሪነቱ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል በአላባ ከተማ የሆነና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በመደበኛ የትምህርት መርሀ ግብር የፊዚክስ ዲፓርትመንት የ3ኛአመት ተማሪ ሲሆን የክረምት የእረፍት ቆይታውን ከቤተሰቦቹ ጋር በማሳለፍ ትምህርቱን ለመከታተል ወደ ዩኒቨርሲቲው ሲመጣ የጥበቃ ሠራተኞች ማንነቱን አረጋግጠው ወደ ግቢ እንዳይገቡ ከተከለከሉ ተማሪዎች አንዱ እንደሆነና ከትምህርት ቤት የተባረረ በመሆኑ ከአካባቢው እንዲርቅ በተነገረው መሰረት አካባቢውን ለቆ መሄዱን እና በምን ምክንያት ሊባረር እንደቻለ አለማወቁን፣ እንዲሁም አቤቱታውን እንኳ ለማሰማት ባለመቻሉ ችግር ላይ እንደሚገኝ አመልክቷል፡፡**

6. **አቡበከር አብዱላዚዝ ነዋሪነቱ በኦሮሚያ ክልልላዊ መንግስት በመርቲ ዞን ነገሌ ቀበሌ 01 ነዋሪና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በመደበኛው ትምህርት መርሀ ግብር የ4ኛ አመት የሂሳብ ተማሪ ሲሆን የክረምት እረፍቱን ከቤተሰቦቹ ጋር በማሳለፍ የ2000 ዓ.ም ትምህርቱን ለመከታተል ወደ ዩኒቨርሲቲው ሲመጣ የጥበቃ ሠራተኞች ማንነቱን አረጋግጠው ወደ ግቢ እንዳይገቡ ከተከለከሉ ተማሪዎች አንዱ እንደሆነ እና ከትምህርት ቤት የተባረረ በመሆኑ ከአካባቢው እንዲርቅ በተነገረው መሰረት አካባቢውን ለቅቆ መሄዱን፣ በምን ምክንያት ሊባረር እንደቻለ አለማወቁን እና አቤቱታውን እንኳን ወደ ግቢው ገብቶ ሊያሰማ ባለመቻሉ ችግር ላይ እንደሚገኝ አመልክቷል፡፡**

ስማቸው ከላይ ከተዘረዘረው በተጨማሪ ሌሎች ዝርዝራቸውን ለጊዜው ማረጋገጥ ያልተቻለ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በተመሳሳይ ሁኔታ ከትምህርት ገበታቸው እንደተባረሩ ኢሰመጉ ተረድቷል፡፡ እነዚህ ተማሪዎች ከትምህርት ገበታ መባረርንና የትምህርት ማስረጃ መከልከልን ያህል ከባድ ውሳኔ ሲተላለፍባችው እንኳን የቀረበባቸውን ማስረጃ የማስተባበልና ይግባኝ የማለት እድል ቀርቶ ክስ የቀረበባቸው መሆኑ እንኳን አልተነገራቸውም፡፡ እንደተባረሩና የተመረቁት ደግሞ የትምህርት ማስረጃ እንደማይሰጣቸው የተወሰነባቸው መሆኑን ያወቁት ወደ ግቢው መግባት እንደማይችሉ በጥበቃ ሰራተኞች ሲነገራቸው ብቻ ነው፡፡ አንድ የዩኒቨርሲቲው ሀላፊ ይህ ለምን ሆነ ተብለው ተጠይቀው ሲመልሱ ውሳኔው የተወሰነው ተማሪዎች ዕረፍት ላይ በነበሩበት ወቅት ስለነበር የቀረበባቸው ክስ ሊነገራቸው እንዳልቻለ ለኢሰመጉ በቃል መልሰዋል፡፡

ይህ ከህግና ከሥርዓት ውጭ የሆነ ውሳኔ ሲወሰን የተማሪዎች ህብረት ያልተሳተፈ መሆኑን ለማወቅ የተቻለ ሲሆን ኢሰመጉ ውሳኔውን አስመልክቶ ከዩኒቨርሲቲው በኩል መረጃ ለማግኘት ኅዳር 3 ቀን 2000 ዓ.ም. በቁጥር ER3-820/1/11/07 በተጻፈ ደብዳቤ የጠየቀ ቢሆንም ምላሽ ማግኘት አልተቻለም፡፡

## ማጠቃለያ

- ከዚህ በላይ በዝርዝር እንደተመለከተው ተማሪዎች ከትምህርት ገበታቸው እንዲባረሩ የተመረቁት ደግሞ የትምህርት ማስረጃ እንዳይሰጣቸው ሲወሰንባቸው የቀረበባቸውን ክስና ማስረጃ የማስተባበልና የመሰማት እድል ቀርቶ ክስ የቀረበባቸው መሆኑ እንኳን አልተነገራቸውም፡፡

- ይህ ደግሞ በአገሪቱ ህገመንግስት የተቀመጠውን የህግ የበላይነትና ህግና ሥርዓት የመከተል ግዴታ (due process of law) በግልጽ የሚጻረር ተግባር በመሆኑ ኢሰመጉ ያወግዘዋል፡፡

- ስለሆነም የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለህግ የበላይነት ተገዢ በመሆን ያለ ህግ አግባብ ከትምህርት ገበታቸው ያባረራቸውን ተማሪዎች በአስቸኳይ ወደ ትምህርት ገበታቸው እንዲመልሳቸው፣ የትምህርት ማስረጃ እንዳይሰጣቸው የከለከከላቸውንም ማስረጃቸውን እንዲሰጣቸው እንጠይቃለን ፡፡

በተጨማሪም ለሰብአዊ መብቶች መከበርና ለሕግ ልዕልና የቆማችሁ ዜጎች፣ ብሔራዊና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች፣ የመንግሥታትና የዓለም አቀፍ ድርጅቶች ተወካዮች የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በአገሪቱ ህገመንግስት የተረጋገጡትን መብቶች እንዲያከብርና ከህግና ሥርዓት ውጭ ከትምህርት ገበታቸው ያባረራቸውን ተማሪዎች በአስቸኳይ ወደ ትምህርት ገበታቸው እንዲመልሳቸው፣ የትምህርት ማስረጃ እንዳይሰጣቸው የከለከከላቸውንም ማስረጃቸው እንዲሰጣቸው የበኩላችሁን ግፊት ታደርጉ ዘንድ ኢሰመጉ ይጠይቃል፡፡

<u>ግልባጭ</u>

- **ክቡር አምባሳደር ተሾመ ቶጋ**
  *የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት አፈጉባኤ*
  *ፖ.ሣ.ቁጥር **80001**፣ ፋክስ **(251-11) 155 09 00***
  *ስልክ **(251-1) 124 10 13***
  *አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ*

- **ክቡር አቶ ደግፌ ቡላ**
  *የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የፌዴሬሽን ም/ቤት አፈ ጉባኤ*
  *ፖ.ሣ.ቁጥር **80001**፣ ፋክስ **(251-11) 155 07 22***
  *ስልክ **(251-11) 124 23 01***
  *አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ*

- **ክቡር አቶ ግርማ ወ/ጊዮርጊስ**
  *የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ኘሬዚዳንት*
  *ፖ.ሣ.ቁጥር **1031**፣ ፋክስ **(251-11) 155 20 20***
  *ስልክ **(251-11) 551 88 50***
  *አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ*

- **ክቡር አቶ መለስ ዜናዊ**
  *የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር*
  *ፖ.ሣ.ቁጥር **1031**፣ ፋክስ **(251-11) 155 20 20***
  *ስልክ **(251-11) 122 67 67***
  *አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ*

- **ክቡር ዶ/ር ስንታየሁ ወ/ሚካኤል**
  *የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የትምህርት ሚኒስትር*
  *ፖ.ሣ.ቁጥር 1367*
  *ስልክ (251-) 155 30 33*
  *ኢ-ሜይል፡* minedu@moe.gov.et
  *አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ*

- **ፕ/ር እንድርያስ እሸቴ**
  *የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፕሬዚዳንት*
  *ፖ.ሣ.ቁጥር 1176 ፣ ፋክስ (251-11) 123 97 68*
  *ስልክ (251-11) 123 97 74*
  *ኢ-ሜይል፡* poffice@aau.edu.et
  *አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ*

- **ክቡር አቶ አሰፋ ከሲቶ**
  *የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የፍትሕ ሚኒስትር*
  *ፖ.ሣ.ቁጥር 1370፣ ፋክስ (251-11) 552 0874*
  *ስልክ (251-1) 551 5099*
  *አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ*

- **ክቡር አምባሳደር ካሣ ገ/ሕይወት**
  *የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር*
  *ፖ.ሣ.ቁጥር 1165፣ ፋክስ (251-11) 645 9290*
  *ስልክ (251-1) 645 9228*
  *አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ*

- **ክቡር አቶ አባይ ተክሌ**
  *የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ዋና እንባ ጠባቂ*
  *ፖ.ሣ.ቁጥር 2459፣ ፋክስ (251-11) 645 9229*
  *ስልክ (251-11) 663 5090፣ 663 5363*
  *አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ*